


ማስታወሻ፡- በኮሌጅ ባቡር ጣብያና በኩዊንስ ፓርክ ባቡር ጣብያ መካከል ነን የምንገኘው።

## እንዴት እንደሚያገኙን፡-

ከያንግ የባቡር ጣብያ መስመር:-

- ኮሌጅ ላይ ይውረዱ (ማስታወሻ፡ የዊልቸይር ተደራሽነት የለውም).
- በኮሌጅ መስመር ላይ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ሄደው በምዕራብ በኩል ወዳለው የቤይ እና ኮሌጅ መንገድ መገናኛ ይሻገሩ።
- ጥቂት ሕንጻዎች ወደ ቤይ ሰሜን ክፍል ሄደው ግሬቫይል መንገድ ይደርሳሉ።
- በግሬንቫይል ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ሂደው ግራ ይታጠፉ።
- 76 ግሬንቫኢል በስተቀኝዎ በኩል ያገኙታል።

ከዩኒቨርሲቲ ባቡር ጣብያ መስመር በኩል:

- በኩዊንስ ፓርክ ማቆምያ ላይ ይውረዱ (ማስታወሻ፡- ይህ ባቡር ጣብያ የዊልቸይር ተደራሽነት አለው)
- በኮሌጅና በኤልዛቤት መንገድ መስመር ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ይሂዱ።
- ወደ ግራ ታጥፈው በኤልዛቤት መንገድ በኩል ወደ ሰሜን አቅጣጫ ወደ ግሬንቫይል መንገድ ይሂዱ።
- ዉመንስ ኮሌጅ ሆስፒታል ያለው 76 ግሬንቫይል ላይ ነው።

## የክሮስ ሮድስ ክሊኒክ

ዉመንስ ኮሌጅ ሆስፒታል የስደተኞች የጤና ክሊኒክ

76 Grenville St., **ሦስተኛ ፎቅ**
**ቶሮንቶ, ኦንታሪኦ** M5S 1B2
**ቀጠሮ ለመያዝ ከፈለጉ በዚህ ቍጥር 416-323-6031 ይደውሉና ቍጥር 2 ጨቍነው ያነጋግሩን።**

WOMEN'S COLLEGE HOSPITAL
Health care for women | REVOLUTIONIZED

76 Grenville Street,
Toronto, ON M5S 1B2
T. 416-323-6400
womenscollegehospital.ca
womenshealthmatters.ca
womensresearch.ca
womenscollegehospitalfoundation.ca

Amharic

# The Crossroads Clinic

## (የስደተኛ የጤና ክሊኒክ)

WOMEN'S COLLEGE HOSPITAL
Health care for women | REVOLUTIONIZED

# The ክሮስሮድስ ክሊኒክ

ወደ ክሮስሮድስ ክሊኒክ – ውመንስ ኮሌጅ ሆስፒታል የስደተኞች ጤና ጉዳይ ክሊኒክ እንኳን ደህና መጡ እንላለን! ስላገኙንም በጣም ደስተኞች ነን!

የሕክምና ባለሙያዎቻችን በመቶ ከሚቆጠሩ አዲስ መጪ ስደተኞች ጋር ብዙ ሠርተዋል። ስለሆነም ስደተኞች ከሚገጥሟቸው ጉዳዮች ጋር ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ናቸው። ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ አስፈላጊውን አገልግሎት ሊሰጡዎት የሚችሉ የዶክቶሮች ጓድና ነርስ ሰራተኞች አሉን። በሐኪም ለመታየት በመጡ ቊጥር ጉዳይዎን ከያዘው ዶክተር ጋር እንዲገናኙ እናመቻቻለን፣ ነገርግን አልፎ አልፎ ከሌላ የሐኪሞች ጓድ ጋር ሊገናኙ ይችላሉ።

አካላዊና ስሜታዊ ሁኒታዊም ሆነ ማንኛውም የጤናዎ ጉዳይ እንመለከታለን። በታመሙ ጊዜ እናይዎታለን፣ ሲታመሙ ብቻም ሳይሆን ቀደም ብሎ ተገቢ ምርመራ በማድረግና አስፈላጊ የሆኑ ክትባቶችንም በመስጠት እንዳይታመሙ ጥሩ እንክብካቤ እናደርግልዎታለን። ከሌሎች የጤና ጉዳይና ማኅበራዊ አግልግሎት ከሚሰጡ ተቋሞች ጋርም እንደአስፈላጊነቱ እንዲገናኙ በማመቻቸት ልንረዳዎት እንችላለን።

ብዙ ልዩ ልዩ አገልግልቶችን እንሰጣለን፣ የሚከተሉትንም ጭምር፦

- እንደ ደም ግፊትና የስኳር በሽታና የመሳሰሉት ሥር-ሰደድ በሽታዎች አያያዝ፣
- ክትባቶችን ጨምሮ ተቀዳሚ የሕጻናት ሕክምና፣
- በእርግዝና ጊዜ እንክብካቤ፣
- የቤተሰብ ዕቅድ ምክር፣
- በሁሉም ዕድሜ ክልል ላሉ ዓመታዊ የጤና ምርመራ፣
- ወደፊት ሊከሰቱ ከሚችሉት በሽታዎች ስለመጠንቀቅ፣
- ስለእንቅልፍ ጊዜ አለመስተካከል፣ የመጨነቅ ሁኔታ እና ውስጣዊ መረበሽ፣
- ምርመራ እና ከባድ ሕመሞች ጉዳዮች የተመለከተ፣
- አስፈላጊ ሲሆን ከባለሙያዎች ቀጠሮችን ስለ ማስያዝ፣
- ስለ ተለያዩ የጤና ጉዳዮች ትምሕርት

ለሁለት ዓመት የሕክምና አገልግሎት እንሰጣለን። ከሁለት ዓመት በኋላ ግን ለመኖርያ ቤትዎ ቅርበት ካለው የቤተሰብ ዶክተር ጋር እንዲገናኙ እናደርጋለን።

በራስዎ ቋንቋ አገልግሎት ልንሰጥዎት እንችላለን፤ እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን በቴሌፎን የቋንቋ አስተርጓሚ አገልግሎት መስጠት እንችላለን።

የጤናዎ ዝርዝር ሁኔታ በግል በምስጢር እንጠብቃለን፣ ያለ እርስዎም ፈቃድ ለማንም ማካፈል አንችልም።

## ቀጠሮ

ቀደም ብሎ በተያዘላቸው ቀጠሮ መሠረት ሕመምተኞችን እናያለን። እባክዎ በቀጠሮ ሰዓት ይገኙ! ምናልባት በቀጠሮዎ ጊዜ መገኘት ካልቻሉ በተቻለ መጠን ቀደም ብለው ይደውሉና ያሳውቁን። አንገብጋቢ ለሆነ የጤና ጉዳይ (ለምሳሌ፦ ትኩሳት፣ ችፍታ፣ ሕመም ወዘተ) አንዳንድ ጊዜ ያለ ቀጠሮም መጥተው እንዲታከሙ ማድረግ እንችላለን። እንዲህ ዓይነቱን አገልግሎት ከፈለጉ እባክዎት በ**416-323-6031 ደውለው ቊ. 2 ይጨቊኑና** ያነጋግሩን።

ከክሊኒካችን ሆነ ከልዩ ባለሙያ ዶክቶሮች ጋር ለእርስዎ ባስያዝነው ቀጠሮ መገኘትዎን እርግጠኛ ይሁኑ። አስፈልጊውን ምርመራ እንዲደረግ ቢታዘዝ የተጠየቁትን ሁሉ ያሟሉ። ከልዩ የጤና ባለሙያ ዶክተር ጋር ቀጠሮ ሲያዘልዎትና ስሊህ ጉዳይ መልዕክት ቢደርስዎት ነገርግን ኢንፎርሜሽኑ ቢደርስዎትና በሚገባ የሚያውቁት ካልሆነ ይደውሉልን ወይም ወደ ክሊኒካችን ይምጡና ስለ ጉዳዩ ማብራርያ እንሰጥዎታለን።

## መታወቂያ

በቀጠሮዎችዎ ጊዜ እና መድኃኒት ሲታዘዝልዎት ጊዜ የስደተኛ መታወቂያና መረጃዎችን ይዘው ይምጡ። የፌደራል ጊዜያዊ የጤና ጉዳይ ፕሮግራም (IFHP), የኦንታሪዮ ሥራ ጉዳይ (OW)፣ የኦንታሪዮ የመድኃኒት ተጠቃሚነት (ODB) መረጃ ወረቀቶችን ይያዙ። በተጨማሪም የኦሂፕ OHIP ካርድዎን (ያልዎት ከሆነ) እና የሶሻል አሲስታንስ እና የመድኃኒት እዝ ካርድ ይዘው ይቅረቡ።

## ከቢሮ ሰዓት በኋላ

ቢሮችን ዝግ ሆኖ እያለ አጣዳፊ የጤና እክል ቢገጥምዎት የሰአቱ ተረኛ ከሆነው ዶክተሩ ጋር መገናኘት ይችላሉ። ስለሆነም በዋናው የክሊኒክ ቴሌፎን ቊጥር ይደውሉና ኦፐሬተሩን ያነገጋሩ፣ መልሶ ሊደውልልዎት ለሚችል ዶክተር ሁኔታዎን በፔጅ አስታላልፎ ያሳውቃል። በጣም አደገኛ ለሆነ የጤና እክል ለምሳሌ እንደ ደረት ላይ የሚሰማ ብርቱ ሕመም፣ የመተንፈስ ችግርና እንዲሁም ሌላ የከፋ ጉዳት ቢደርስብዎ በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ ሆስፒታል የድንገተኛ አደጋ ክፍል (ኢመር ገንሲ) ቶሎ ይሂዱ።

## አድራሻችንና ቊጥራችን

76 Grenville St., 3rd floor
Toronto, ON M5S 1B2

## የሥራ ሰዓቶች

**ከሰኞ እስከ ዓርብ, ከጠዋቱ 9 a.m. እስከ ከሰዐት 4 p.m.**

ቀጠሮ ለመያዝ ከፈለጉ በዚህ ቊጥር **416-323-6031 ደውለው ቊጥር 2ን በመጫቆን** ያነጋግሩን።.